# ቁ ዘ ማ

ሻቢያ ወያኔ ቤቴን ቢሞላው
እኔ ምን አባቴን ውጭ ልኑረው ፡፡
አይዞሽ ያገሬ ልጅ ግድ የለም ግድ የለም
ኢትዮጵያዊነትን የሚነጥቀን የለም ።
ኢትዮጵያ ምንጫችን ሁሌ የምንጠጣት
ወያኔ ገባና አደፈረሳት ።
ተው ተው አትበሉት የልቡን ያድርሰው
ጀግና ከተነሳ መመለሻም የለው ።

ተወው ተወው አለኝ እኔ እንደምን ልተው
ደም ማፍሰስ አባዜ እንደ ቅል የነፋው ።

ወያኔውም ዕውር ካድሬውም ዕውር
ሻቢያውም ዕውር ሁላቸው ድንብርብር
እረ ለስንታችው ይቆረሳል አገር ።

የወያኔ ሽታ
ዘላለም በሽታ ።

የጋኔን ዘመድ ነው የይሁዳ ልጅ
መሀላችን ገባ ህዝቦችን ሊፈጅ ።

ኢትዮጵያን አፍርሱ ይላል በትግሪያ
የሻዕቢያ ወንድም የጋኔን መንትያ ።

ባሰላው ባሰላው እንቢ አለኝ ይዘቱ
ከታችም እማይደል ከላይ ነው ስህተቱ ።

ስም በከንቱ አይወጣም ብርቱካን ተባለች
ቀደም ቀደም ብላ ታሳየን ጀመርች ።
ስም በከንቱ አይወጣም ቴዎድሮስ አሉህ
ቀድሞ ቢታያቸው ውድ ወላጆችህ ።

ከት ከት ብላ ሳቀች ምድር አፍ አውጥታ
ጀግና እየታሰረ ባንዳ እየተፈታ ።

**ክንፈ ሚካኤል**
**ሜልበርን፣ አውስትራሊያ**
**ሰኔ ፲፫ ቀን ፪ሺህ፭ ዓ/ም**